ቀን፡ ታህሳስ 11/2000 ዓ.ም
ቁጥር፡ ቅአዴ/0101/2000

ከሀገር ውጭ ለምትገኙ
የላዕላይ ም/ቤት አባላት በሙሉ
በያላችሁበት

ጉዳዩ፡ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የላዕላይ ም/ቤት ስብሰባ ጥሪን ስለማሳወቅ

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ታህሳስ 11 ቀን 2000 ዓ.ም ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ የፓርቲው የላዕላይ ም/ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ በመስማማት የሚከተለውን ውሳኔ አስተላልፏል።

1. የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የላዕላይ ም/ቤት አስቸኳይ ስብሰባ እሁድ ታህሳስ 13/2000 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ይካሄዳል። በዕለቱ ምልዐተ ጉባኤ የሚሟላ ከሆነ ም/ቤቱ በተያዘው አጀንዳ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ያስተላልፋል።
2. ከላይ በተጠቀሰው ዕለት ምልዐተ ጉባኤ ካልተሟላ ላዕላይ ም/ቤቱ በድጋሚ ስብሰባውን ቅዳሜ ታህሳስ 19 ቀን 2000 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ከ8፡00 ጀምሮ ያካሄዳል። በቀረበው አጀንዳ ላይም ተወያይቶ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል።
3. ታህሳስ 19 ቀን በተጠራው ስብሰባ ምልዐተ ጉባኤ ካልተሟላ እሁድ ታህሳስ 20 ቀን 2000 ዓ.ም ከጥዋቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ የላዕላይ ም/ቤት ስብሰባ ይካሄዳል። በዚህ ዕለትም በተገኙት አባላት በተያዘው አጀንዳ ላይ ውይይት ተደርጎ ገዢ(binding) ውሳኔ ይተላለፋል።

በመሆኑም እርስዎ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ የላዕላይ ም/ቤት አባል በመሆንዎ ከላይ በተጠቀሱት ቀናት በስብሰባው እንዲገኙ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል።

ከሰላምታ ጋር

ሙሉነህ ኢዮኤል
የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
ዋና ጸሐፊ